## ምድብ ሁለት (ከ1ኛ — 3ኛ) ክፍል

## 26 ኛ ሳምንት

# ልጆች ክርስቶስን ተቀበሉት

**ዓላማ**

❖ ክርስቶስ በክብር ወደ ኢየሩሳሌም መግባቱንና እንዴት እንደተቀበሉት መማር።

**ምንባብ**

❖ ማቴ. 21÷1-15

**መግቢያ**

❖ ንጉሡ ዳዊት ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ላይ ተጭኖ እንደሚመጣ ተንብዮአል።
❖ ዛሬ የምንማረው ታሪክ የትንቢቱን ፍጻሜ ይሆናል።
❖ ዳዊት ሕጻናት እንዴት እንደሚቀበሉት የተነበየውንም እንማራለን።

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1.ጌታችን ኒቆዲሞስን ምን አስተማረው?

2. ጥምቀት ምንድነው?

**ትምህርቱ**

❖ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ብዙ ተዓምራት ፈጽሞል።አዎን እርሱ ሽባውን እንዲራመድ፣እውራኑ እንዲያዩ፣የማይሰሙት እንዲሰሙ አድርጓል።
❖ አንድ ቀን÷አይሁድ በኢየሩሳሌም በዓል የሚያከብሩበት ቀን ነበርና ብዙ ሕዝብ ለበዐሉ ተሰባስበው ነበር፤ክርስቶስም በአህያ ተጭኖ ወደ ኢየሩሳሌም ገባ።
❖ ብዙ ተዓምራት ሲያደርግ ይሰሙ ስለነበር አልኣዛርን ከሞት ማስነሳቱም ስለተሰማ።ዮሐ.11÷1-ፍጻሜ ምዕራፍ ለበዐል የተሰበሰቡት ሕዝብ ክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣቱን ሲሠሙ ሊቀበሉት፣ሊያዩትም ወጡ።
❖ ጌታችን በአህያይቱ ላይ ተጭኖ ሲገባም፣የዘንባባ ዝንጠፊ፣የዛፍ ቅጠል ጫፍ፣ ልብሳቸውንም እያነጠፉ በክብር ተቀበሉት።
❖ በዚህ ዕለት ልጆች፣በእናታቸው እቅፍ የተያዙ ሕጻናትም ሊያዩት መጥተዋል። እንዲህ ሲሉም ዘምረዋል።« *በጌታ ስም የሚመጣ የተባረከ ነው፤ ሆሣዕና በአርያም።*»
❖ ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ ጌታችንና መድኃኒታችን የመረጣቸው የሆነውን በመጀመሪያ አላስተዋሉም ነበር። በኋላ ግን ነቢያት ቀድመው ተንብየው እንደነበርና ያም መፈጸሙን አስተዋሉ።
❖ ነቢይናመዝሙረኛው ዳዊት«*ከሕፃናትና ከሚጠቡ አፍ ምሥጋናን ለራስን አዘጋጅህ*»መዝ.8÷2 ሲል ቀድሞ ተንብዮ ነበር።
❖ ነቢዩ ዘካርያስም *«ለጽዮን ልጅ፡-እነሆ÷ንጉሥሽ የዋህ ሆኖ በአህያ ላይና በአህያይቱ ግልገል በውርንጫይቱ ላይ ተቀምጦ ወደ አንቺ ይመጣል በሉኣት»* ትን.ዘካር. 9÷9 ተብሎ የተነገረው ተፈጸመ።

**ጥያቄ**

1.ጌታችን ወደ ኢየሩሳሌም ሲመጣ ሕዝቡ ምን በማድረግ ተቀበሉት?

2.ለምን ይሄን አደረጉ?

3.ጌታ ወደ ኢየሩሳሌም የገባው በምንድነው?

4.ሕዝቡና ሕፃናት ምን ብለው ዘመሩ?

5.ስለክርስቶስ ወደ ኢየሩሳሌም መምጣትና ልጆች እንደሚዘምሩለት የተነበዩት እነማን ናቸው?

**መዝሙር**

ሆሣዕና በአርያም

እያሉ ዘመሩ ሕፃናት በኢየሩሳሌም

**ይቆየን።**